# የቃላት ቋጠሮዎች

አብርሃም በየነ

ድርጊቱ ሲያስደስት እርካታው ሲጎላ

ልብ ያላሉት ነገር አእምሮና ገላ

የጀማ ፍርድና የማሸላ ጠላ

እራስ ላይ ይደርሳል ቆይቶ ወደ ኋላ።

..................................................................

በቅቡል አንደበት በቃላት ሞሽሮ

ወይም በልብ ወለድ በማስመሰል ፈጥሮ

ዓመኔታ እሚቀርጽ ምንም ይሁን የትም

ዕውነት እንደ ውሸት ብዙ መልክ የላትም።

...........................................................................

ፖምና መንደሪን እንጆሪ መስለሽኝ

ልገምጥሽ ጓጉቼ ሳይሽ አሳስተሽኝ

አበባ ሆንሽና ቀረሁ እንዳማርሽኝ።

................................................................

አክበህ ኩብኩበህ ያሳደከው ቡድን

የጎጥ አጋሚዶ ሰው እንደ አውሬ ሲያድን

በዕብሪት ተወጥሮ በለገስከው ቅልጥም

በሌላው ኪሳራ ያንተን ዘር ሲጠቅም

ተው ባለማለትህ ሕዝቢ ደቅ ትግራይ

አንተነህ እወቀው የርሱን ዕዳ ከፋይ።

....................................................................

የሰው ልጅ በበጎም ይሁን በመጥፎ ምግባሩ መስፈርት ሲሰፈር

ዓለም ያወቀው የታሪክ ፍራሽ አዳሽ ስለሆነ በባህሪው አፈጣጠር

ታሪክ ራሷን ትደግማለች መቼም ይሁን የትም አገር።

መስከረም 2005

................................// ................................